## መንፈስ፣ መንፈስ-ቅዱስ፣ መንፈስ-ርኩስ።

### መንፈስ።

እውነት፡ በባሕሪዋ ግልጽ፣ የማትለዋወጥ፣ ምንታዌነትና ርባኤ የሌላት ስለኾነች፡ ልትሰወር ወይም ልትጠፋ ከቶ ኣትችልም። በዚህ ባሕሪዋ ምክኒያት ነው፡ ሰዎች በጊዜና በቦታ ርቀት ምክኒያት፡ ያላዩኣቸውንና ያልሰሟቸውን ኹኔታዎችና ድርጊቶች እንኳ ሳይቀር፡ ኹኔታዎቹ ሲደረጉና ሲፈጸሙ፡ ንቁ ሳይኾኑ እያዩና እየሰሙ ከነበሩት ይልቅ፡ የበለጠ እንዲገነዘቡና እንዲረዱ የሚያደርጋቸው። ማለትም፡ ስለኣንድ የተወሰነ ድርጊት ወይም ኹኔታ፡ የኣፈጻጸም ምንነት፣ ማንነት፣ እንዴታነት፣ ወዘተ ለማወቅ፡ የሚያስፈልጉት ክህሎቶች፡ ባጭር ታጥቆ መገኘትና የእውነት ዕውቀትን መያዝ ናቸው።

ዳግመኛም፡ በግዙፉ ዓለም ያሉ እውነታዎች፡ በረቂቁ ዓለም ያሉትን እውነታዎች የሚያስረዱና የሚገልጡ ኾነው እናገኛቸዋለን። የዚህን ኣባባል እውነታነት በኣጽንዖት ለማስገንዘብ ይመስለኛል፡ ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮጵያዊያት የሚከተሉትን ጽንሰ-ሓሳቦች ገልጠው በኣጽንዖት የሚያስገነዝቡት፤ “እግዚኣብሔር ሰውን በኣርኣያውና በኣምሳሉ ፈጠረው!” *[ይህ ኣባባል፡ ሰዎች ረቂቅና ምጡቅ ስለኾነው፡ ስለፈጣሪያቸው እግዚኣብሔር ምንነትና ማንነት፡ ሊረዱና ሊገነዘቡ የሚችሉት፡ በግዙፍ ሊያዩትና ሊከታተሉት ከሚችሉት ከራሳቸው ምንነትና ማንነት ግንዛቤ መኾኑን የሚያመለክት ነው።]*፣ “ተሠርዐ በምድር ተሠርዐ በሰማይ *(ይህ ኣባባል እርማት ያስፈልገው ይኾናል!)*- ማለትም፡ በሰማይ ተሠርቶ የሚገኘው፡ በምድር እንደሚገኘው ዓይነት ነው!” *[በረቂቁ ዓለም የሚገኘው ሥርዓት፡ በግዙፍ ዓለም ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ስለኾነ፡ የግዙፉን ዓለም መገንዘብ፡ የረቂቁን ዓለም ለመገንዘብ ያስችላል የሚል ኣባባል ነው።]*

በነዚህ ኹለት ኣንቀጾች ውስጥ የተጠቀሱት፡ የእውነት ባሕርይና የግዙፉና የረቂቁ ዓለም የዝምድና እውነታ፡ ስለመንፈስ ምንነትና ማንነት የሚደረገውን ሓተታ(ምርምር) ቀልጣፋና ግልጽ ያደርጉታል ተብሎ ስለታመነባቸው ቀድመው እንዲገለጹ ኾነዋል።

ግዙፉን ፍጥረታት ማለትም ጠጣር፣ ፈሳሽና ትነት(ነፋስ)[፩]፡ ካንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፤ ይዘዋወራሉ። የነዚህ ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴዎች ሥያሜም፡ ለጠጣሮቹ፡ መሄድ (መብረር፣ መራመድ፣ ወዘተ)፣ ለፈሳሾቹ፡ መፈሰስ ሲኾን፡ ለትነት (ለነፋስ) ደግሞ፡ መንፈስ[፪] የተባሉት ናቸው።

ረቂቅ በኾነው በነፍስ ዓለም ውስጥም እንቅስቃሴዎች ኣሉ። ከእንቅስቃሴዎቹ መካከል ኣንዱ፡ የዕውቀት እንቅስቃሴ ነው። ዕውቀት የሚባለው የነፍስ ባሕርይ፡ ካንዱ ነፍስ ወጥቶ ወደሌላ ነፍስ ይሄዳል፤ ይንቀሳቀሳል፤ የዕውቀት እንቅስቃሴ ግን በግዙፉ ዓለም እንዳለው ዓይነት እንቅስቃሴ ኣይደለም። በግዙፉ ዓለም ያለው እንቅስቃሴ፡ ካንድ ውስን ቦታ ወደሌላ ውስን ቦታ የሚደረግ፡ እንቅስቃሴ ነው። የዕውቀት እንቅስቃሴ ግን፡ ኣንድ ነፍስ የራሷን የሚያኽልና የሚመስልን ዕውቀት፡ በሌላ

---

*[፩] ትነት(ነፋስ)፡ ረቂቅነቱ ለዓይን እንጂ፡ ለኹሉም የስሜት ሕዋሳት ኣይደለም። ሲጮህ እንሰማዋለን፣ ሰውነታችንን ሲዳስሰን ይታወቀናል፤ ግዙፍ ፍጥረት መኾኑ በዚህ ይታወቃል*

*[፪] ፈሰሰ ብሎ መፍሰስ ካለ፡ ነፈሰ ብሎ መንፈስ መባሉን ማስተዋል ያስፈልጋል።*

ነስፍ ውስጥ እንዲገኝ ማድረግ ነው። የዚህ እንቅስቃሴ ባሕርይ ከመሥረጽ[፫] ጋር ይመሳሰላል። ነፍስ በባሕሪዋ ዕውቀት ከራሷ ማሥረጽ(ማንቀሳቀስ) ትችላለች። የዕውቀት ባሕርይ ደግሞ፡ ካንዱ ነፍስ ወደሌላ ነፍስ መንቀሳቅስ(መሥረጽ) ነው። ይህ እንቅስቃሴ፡ በባሕሪው ረቂቅ ስለኾነ፣ ይህንን ባሕሪውን ይገልጻል ተብሎ በታሰበው፡ በዚህ ግዙፍ ዓለም ላይ፡ ለዕይታ ረቂቅ በኾነው በነፋስ እንቅስቃሴ ተወክሎና ተሠይሞ ተቀምጧል። ስለዚህ፡ ዕውቀት፡ ካንድ ነፍስ ወጥቶ ወደሌላ ሲሄድ፡ "ነፈሰ" የሚባል ሲኾን፡ ያ የወጣው ዕውቀት ደግሞ፡ "መንፈስ" ይባላል።

ጸሐፈ ብሎ መጻሓፍ፣ ዘመረ ብሎ መዝሙር ካለ፡ ነፈሰ ብሎ መንፈስ ይላል፡ የልሳኑ ሥርዓት። መጽሓፍና መዝሙር ኣስገኚዎቻቸው ከኾኑ ኣካላት ተጽፈውና ተዘምረው ወይም መንጭተው እንደተገኙና የኣስገኚዎቻቸውን ኣስተሳሰብ ወይም ምንነትና ማንነት እንደሚገልጹ ኹሉ፡ መንፈስም እንደዚሁ ነው።

ነፍስ፡ ዕውቀት ወይም መንፈስ የምታሠርጸው፡ በነባቢነት ባሕሪዋ ነው። "ነበበ" ማለት ተናገረ ማለት ሲኾን፡ ሰዎች ዕውቀታቸውን በብዙ መልክ ይናገራሉ ወይም ይገልጣሉ። በጽሑፍ፣ በንግግር (በውይይት)፣ በሥዕል፣ በድርጊት፣ በተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችና በመሳሰሉት። ለምሳሌ፡ ኣንድ ሰው መጽሓፍ ጻፈ ወይም መገልገያ ቁስ ሠራ እንበል። ያ ግለሰብ፡ መጽሓፉን ከመጻፉ ወይም መገልገያ ቁሱን ከመሥራቱ በፊት፡ እንዴት፣ ለማን፣ ለምን እንደሚያደርገው ኣስቦበታል። ከዚያም፡ መጽሓፉ ተጽፎ ለንባብ እና መገልገያ ቁሱም ተከውኖ ለኣገልግሎት ሲበቃ፡ ያ ሰው "ተናገረ" (ነበበ) ይባላል ማለት ነው። ሰዎች፡ መጽሓፉን ኣንብበው፡ የመገልገያ ቁሱንም ኣይተዉትና ተገልግለውበት፡ ከዚያ ያገኙትን ዕውቀት፡ ዕውቀታቸው ኣድርገው ሲጠቀሙበትና ሲገለገሉበት፡ ዕውቀት ከጸሓፊው ወይም ከኣናጺው ነፍስ ሠርጾ፡ ወድሌላ ነፍስ ሄደ፣ ገባ እንላለን ማለት ነው። በዚህም ምክኒያት፡ የጽሑፍ ድጉስ መጽሓፍ እንዲባል፡ የንፋስ ድጉስም መንፈስ ተብሏል። ይህንን ኹኔታ ጊዜና ቦታ ስይገድበው ይኖራል፤ በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜዎች የምንኖር እኛ ሰዎች ዕውቀት ስንቀባበል ኖረናል፣ እንኖራለንም።

"ሰው በእግዚኣብሔር ኣርኣያና ኣምሳል ተፈጠረ!" ከተባለው ማስገንዘቢያ ኣንጻር ስንገመግመው፡ በእግዚኣብሔር በኩል ያለውንም ስናስበው የምናገኘው እውነታ ተመሳሳይ ነው። እግዚኣብሔር፡ ሥነ-ፍጥረትን ከመፍጠሩ ኣስቀድሞ፡ ሥነ-ፍጥረትን ለምን፣ እንዴት መፍጠር እንዳለበት ኣስቧል። ከዚያም ፈጥሯል። ይኸው ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ፡ ከዚህም በኋላ እስከዘላለም፡ ያ ሥነ-ፍጥረትን የፈጠረበት ዕውቀት፡ በሥነ-ፍጥረት ኣማካኝነት ወደፍጥረቱ ሲሠርጽ ይኖራል። ሰዎችና መላእክት ይህንን ኹኔታ በጥልቀት እንዲረዱና እንዲኖሩበት ኾነው እንደተፈጠሩ፡ ኹሉም በየራሱ የሚኾነውን ኹኔታ በንቃት በመከታተል ማወቅ ይችላል። ከመላእክትም ይልቅ ሰዎች ደግሞ፡ የበለጠ ዕድልና ጸጋ የተሰጣቸው እንደኾኑ፡ ማወቅና መረዳት ይቻላል፤ ይኸውም፡ የሰው በሥጋ ገዝፎ፡ በዚህ በግዙፉ ዓለም እንዲኖር ያስቻለው፡ የመኖር ሥጦታ ወይም ጸጋ ነው።

[፫] *ሠሪጽ፤ ጾት፤ (ሠረጸ፣ ይሠርጽ፣ ይሥረጽ። ዕብ፡ ሻራጽ)፤ መፍላት፣ መውጣት፣ መብቀል፣ ሥር መስደድ፣ መለምለም፣ ማፈጥፈጥ፣ የተሓዋሲያን የኣዝርዕት፣ የኣትክልት። ኪዳነወልድ ክፍሌ (፲፱፻፵፰ ዓ.ም.) መጽሓፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሓዲስ፤ ገጽ ፮፻፸፱።*

## *መንፈስ-ቅዱስ።*

ይህ ከፍጥረቱ ወደፍጥረቱ የሚሠረጸው መንፈስ (ዕውቀት)፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም መንፈስ-ቅዱስ[፩] ይባላል። ይህ መንፈስ፡ ኣስቀድሞም ሥነ-ፍጥረትን ለማስገኘት ያሰበው፣ ከዚያም ሥነ-ፍጥረትን የፈጠረውና እውነት ብለን የሠየምነውና የምንጠራው ዕውቀት ነው።

ይህንን መንፈስ (ዕውቀት) "እሺ!"፣ "ይበጀኛል!" ብለው የተቀበሉ ሰዎች፡ ኣስተሳሰባቸው፡ እውነተኛና ቀና፡ ኑሯቸው ወይም ምግባራቸው የጽድቅ ነው፤ ማለትም እንደእግዚኣብሔር ነው፤ ምክኒያቱም በኣንድ ዓይነት ዕውቀት(መንፈስ) ነውና የሚመሩት። ስለዚህ፡ ሰዎች፡ መልካም ሥራን ለመሥራት፡ እርስበርስም ተግባብተው፡ እንደኣንድ ሰው፡ ማለትም "እንደኣንድ ልብ መካሪ እንደኣንድ ኣፍ ተናጋሪ" ሊኾኑ የሚችሉትና ኾኑ የሚባለው፡ በንቃት የመኖር ጸጋቸውን በመጠቀም፡ ኣንድ በኾነው በእግዚኣብሔር መንፈስ (መንፈስ-ቅዱስ) ኣምነው ሲገኙና በምግባር ሲኖሩበት ብቻ ነው።

የእውነት ዕውቀት የእግዚኣብሔር ስለኾነች፣ ሥነ-ፍጥረትና ያስገኘችና የምትመራ በመኾኗ፡ ዘለዓለማዊት፣ የማትለዋወጥና አሸናፊ ናት። እርሷ በሌለችበት ብቻ ነው ሌሎች ዕውቀቶች የሚኖሩት። እርሷ በመጣች ጊዜ ሌሎቹ ኹሉ ይጠፋሉ፤ ወዳለመኖር ይመለሳሉ፤ ልክ ድቅድቅ ጨለማ በፍንጣቂ ብርሃን እንዲሚወገድ። ስለዚህ የከፋት ኣበጋዞች የሚያደርጉት፡ የእውነት ዕውቀት በትንሹም ቢኾን እንዳትነገር፣ እንዳትሰማ፣ እንዳትታይ፣ እንዳትተገበር ማድረግ ነው፤ ምክኒያቱም እርሷ መታየት ከቻለች ሌሎቹን ኹሉ ታጠፋለችና።

## *መንፈስ-ርኩስ።*

ከሰዎች ወይም ከመላእክት የሚሠርጹና መከራንና ሥቃይን፡ ባጠቃላይ ሥነ-ፍጥረትን የማይጠቅሙና የሚጎዱ ዕውቅቶች ናቸው። እነዚህ ዕውቀቶች(መንፈሶች)፡ በባሕሪያቸው መከራንና ሥቃይን የሚያመጡ ስለኾነ መንፈስ-ርኩስ ሲባሉ፣ የእውነት ዕውቀት ባለበት ፈጽመው ሊገኙ የማይችሉ፣ ደካማ፣ ኹሌም ተሸናፊዎች ናቸው። ርኩሳን ዕውቀቶች እነዚህን ባሕሪያት የያዙበት ምክኒያት፡ ፍጥረታት እንዲፈጠሩ የወጠነውን፣ ያደረገውንና የሚመራውን የእውነት (የእግዚኣብሔር) ዕውቀት የማይቀበሉ፡ ከዚያም ኣልፎ የሚቃረኑ ስለኾነና፡ ከዚህም ኣፈጣጠራቸው የተነሣ፡ የሥነ-ፍጥረትን መልካም የኣኗኗር መስተጋብር ጊዜያዊ በኾነ ኹኔታ የሚያበላሹና፣ እንደገና ተመልሰው፡ ቋሚ በኾነው በሥነ-ፍጥረት ሥርዓት የሚወገዱ በመኾናቸው ነው። ለዚህ ኣባባል፡ ዓይነተኛ ምሳሌ ኾኖ ሊቀርብ የሚችለው፡ የሰዎች መንግሥት ራሱን የሚመራበት መንፈስ ነው፤ ይኸውም ራሱን እንደእግዚኣብሔር ኣድርጎ ማቅረቡና የሰዎችን ተፈጥሯዊ ጸጋዎች(መብቶች) ኹሉ ኣፍኖና ረግጦ በመያዝ፡ ይህችን ውብና ኣስደሳች ዓለም የመከራና የሥቃይ የማድረጉ ነገርና ይህ ሰብኣዊ ቀንበር(መንፈስ) ገዢ ኾኖ የሚቆየው፡ በሥሩ ተገዝተው የሚኖሩ ሰዎች የእውነትን ዕውቀት እስኪያውቁ ድረስ ብቻ የመኾኑ ነገር ነው።

ነገር ግን የሰዎችም የመላእክትም ታሪክና ኣኗኗር እንደሚያሳየው፡ እነዚህን ርኩሳን ዕውቀቶች መርጠው የኖሩባቸው ጊዜያት እንደነበሩና በተለይም በሰዎች በኩል ደግሞ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመምጣቱን ኹኔታ ነው። ነገር ግን፡ የርኩስ-መንፈስ ተቀባይነት የቱንም ያኽል ቢጨምር፡ የእውነት ዕውቀት በወጣች ጊዜ መጥፋቱ ስለማይቀር፡ ጊዜያዊ ነው።

---

*[፩] ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ስለኾነ፡ ከሰው የተለየ፣ የፈጣሪያችን የእግዚኣብሔር መንፈስ ለማለት ተፈልጎ ነው።*

## የመንፈስ በዚህ መልክ መተርጎም የሚያስገኛቸው ጥቅሞች።

በመሠረቱ፡ ሰዎችም መላእክትም የሚኖሩት መንፈሳቸውን (ዕውቀታቸውን) ነው። መልካም መንፈስ ያላቸው መልካም ኑሮን ሲኖሩ ርኩስ መንፈስ ያላቸው ደግሞ የመከራና የሥቃይ ኑሮን ይመራሉ። ይህ ኣባባል የሚያገለግለው ለሰዎችና ለመላእክት ብቻ ነው። ምክኒያቱም እነዚህ ፍጥረታት፡ መንፈስን(ዕውቀትን) የመቀበልና ያለመቀበል፣ የመመርመርም ጸጋ ያላቸው ፍጥረታት ስለኾኑ ነው። ከዚህ ኣፈጣጠራቸው የተነሣ፡ እነዚህ ፍጥረታት፡ ታላቅ ኃይል ያላቸው ናቸው። በዚህም ኃይላቸው፡ የፈለጉትን፣ ይጠቅመናል፣ ያስደስተናል ያሉትን እንዲያደርጉ እንጂ፡ ኃይል እንዲሌላቸው ኾነው፡ ለእያንዳንዱ ፍላጎታቸው፡ ፈጣሪ እግዚኣብሔር እንዲያሚላላቸው እየለመኑ፣ እየተማጸኑ፣ ጊዜ እያጠበቁ እንዲኖሩ ኣይደለም። እግዚኣብሔር ሥነ-ፍጥረትን የሠራበትና የሚስተዳድርበት መርኅም እንደዚህ ዓይነት ኣይደለም። ይህ የተሳሳተ ኣስተሳሰብ (መንፈስ)፡ ክፉዎች ሰዎች ሃይማኖትን ሲፈጥሩ ኣብረው የፈጠሩት ይመስለኛል። ምክኒያቱም፣ ታሪክና ኣሁንም እውን ኾኖ የሚታየው ኹኔታ እንደሚያሳየን፡ የሃይማኖት መፈጠር ዋና ዓላማ፡ ሰዎችን በሰው መንግሥት ሥር እንዲተዳደሩ ማድረግ በመኾኑ፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት፡ ቀዳሚ መኾን የሚገባው ደግሞ፡ ሰዎች በተፈጥሮ የተለገሷቸውን ኃይል (የማወቅና የመወሰን ጸጋ) እንዳያምኑበት፣ እንዲሁም እንዲንቁት ማድረግና በዚያ ፈንታ፡ የሚያውቅላቸውና የሚወስንላቸው እግዚኣብሔር እንደኾነ ኣድርጎ ማሳመን በመኾኑ ነው። ነገር ግን፡ እግዚኣብሔር ሥነ-ፍጥረትን የሠራበትና የሚያስተዳድርበት መርኅም እንደዚህ ዓይነት ኣይደለም። ይህ ኣስተሳሰብ፡ እውን፣ ማለትም ሊጨበጥ፣ ሊዳሰስ፣ ሊተገበር ኣይችልም። እውን ኾኖ የምናየው ኣሠራር፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በዕውቀቱ ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ እየሰጠ የመኖሩን ኹኔታ ነው።

ከራሴ የሕይወት ልምድ እንደምረዳው፡ ለዚህ ይመስለኛል፡ ባሁኑ ጊዜ በሃይማኖት ተቋማት ኣስተምህሮ ተኮትኩተው ያደጉ ብዙ ሰዎች፡ በንግግርም፣ በጽሑፍም ወይም በሌሎችም ዘዴዎች፡ የኣስተሳሰብ ውይይት ወይም ምክክር በሚደረግበት ጊዜ፡ የኣስተሳሰቡን (የዕውቀቱን) እውነተኛነት ወይም ኣሳማኝነት ከመገምገም ይልቅ፡ ካደጉበት የሃይማኖት ተቋም በይፋ ትእዛዝ የመገኘት ያለመገኘት ኹኔታውን ብቻ በመገምገም፡ የውይይቱን ሓሳብ፡ እንዲሁ ቅቡል ወይም ውድቅ የሚያደርጉት። በዚህ ድርጊታቸውም፡ የሃይማኖት ተቋሙ፡ ምን እንዲኾኑ ኣድርጎ እንዳሠለጠናቸው፡ ማለትም፡ በተፈጥሮ የተለገሳቸውን፣ ማንም ሊወስድባቸውና ሊነጥቃቸው የማይችለውን፣ የራሳቸውን፣ ኹሉን ማደረግና መኾን እንዲችሉ የሚያስችላቸውን ጸጋቸውንና ሥልጣናቸውን እንዲንቁትና እንዲተዉት መኾኑን በግልጽ ያሳያል፣ ይመሰክራል።

እግዚኣብሔር ለፍጥረቱ ኹሉ ፍጹም ነጻነትን ሰጥቷል ሲባል በተለይ በሰውና በመላእክት ላይ ስንመለከተው፡ ፍጽምነቱ ከሚረጋገጥባቸው መንገዶች ኣንዱ፡ ዕውቀት የመቀያየርን፣ ኣንዱን ዕውቀት ትቶ ሌላ የመቀበልን፣ በዚህም የተነሣ፣ በልማድም ኾነ በማወቅ፡ የመሳሳትንና የማጥፋትን ውሳኔን ያከበረ፣ ያረጋገጠ መኾኑ ነው። ይህ ኣባባል እውን ለመኾኑ፡ የሌላ ሰው ምስክርነት ኣያስፈልገውም፤ እያንዳንዱ ሰው ሕይወቱን የሚመራበትን የኣስተሳሰብ ኹኔታ ቢገመግም፡ የሚደርስበት እውነታ ነው። ይኸውም፡ በተለያዩ ኣስገዳጅ ኹኔታዎች ውስጥ ካሉ ሰዎች በስተቀር፡ ሰዎች ኹሉ፡ የሚያስቡትና የሚያደርጉት፡ በየራሳቸው ያመኑበትን ብቻ ከመኾኑም ባሻገር፡ በየቅጽበቱ በመቀያየር፣ በማሳደግ ወይም በማሻሻል ነው። በግል፣ በባልና ሚስት፣ በቤተሰብ፣ በጉርብትና፣ በኅብረተሰብ፣ በኣገር ኣቀፍና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ፡ ተፈጥረው የሚገኙና ኣሁንም እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች፡ ዋና መንስኤያቸው፣ የችግሮቹ ሥር፣ ይህንን የመሳሳትንና የማጥፋት መብትንም ጭምር የሚያካትተውን የተፈጥሮ ነጻነትን ኣለማወቅና ኣለማክበር ነው። ስለዚህ፡ ሰውን፣ እያንዳንዱን፡ ፍጹም ጤነኛና ሰላማዊ ሊያደርግ፣ እርስበርስም ሊያስማማና ሊያግባባ የሚችለው፡ በዚህ እውነት ላይ የተመሠረተ፡ የኣኗኗር ስልት ሲኖር ነው።

ከመላእክትም ይልቅ ሰዎች ደግሞ፡ የሥነ-ፍጥረት ጸጋዎችን እየመረመሩ ፍጹምና ዘለዓለማዊ ደስታን ኣግኝተው እንዲኖሩ፡ ጸጋው የበዛላቸው ናቸው። ሰዎች፡ በዚህ ተፈጥሯቸው፡ ፍጹም በኾነ የማሰብና የመኖር ነጻነት፡ ተድላን፣ ጤናን ሰላምን ኣግኝተው፡ በደስታ መኖር ሲገባቸው፡ ነገር ግን በዚያ ፈንታ በኣመዛኙ የታየባቸውና የሚታይባቸው፡ በራሳቸው የመኖር ጸጋ (ኣስተሳሰብና ፍላጎት) የፈጸሟቸውን ኹሉ፡ ለእግዚኣብሔር በመስጠት፡ “ክፉ ክስተት ነው!” ላሉት እርሱን ተወቃሽ፡ “መልካም ነው!” ላሉት ደግሞ፡ ተመስጋኝ፤ እንደገናም፡ ስንፍናን መቀበል ያልፈለጉ እንደኾነ ደግሞ፡ “የእግዚኣብሔር ፈቃድ ኣይደለም ማለት ነው!” የሚል እምነት በመያዝ እግዚኣብሔርን ተወቃሽ ማድረግ ነው። የዚህ ዓይነቱ ኣስተሳሰብ፡ በተለይም በሃይማኖት ተቋም ውስጥ ባደጉ ሰዎች ላይ የሚታይ፣ ሌላኛው ሊትተው የሚገባው መንፈስ ነው።

በሌላ በኩልም፡ እነዚሁ ሰዎች፡ ፆም፣ ጸሎት፣ ስግደትና የመሳሰሉት፣ በሱባኤ ሊከናወኑ የሚችሉ ረቂቅ የትሕርምት[፭] መንገዶች፡ ዕውቀትን በትዕግስት እንዳንከታተል ያደረጉንን ጎጂ ልማዶችን ማስወገጃ ስልቶች እንጂ፡ እግዚኣብሔር ከኛ የሚፈልጋቸው የኣምልኮ መግለጫዎች እንዳልኾኑ ያለመገንዘባቸው ጉዳይ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ነው። በዚህም ምክኒያት፡ እነዚሁ ሰዎች፡ በዕውቀታቸው ማነስ ምክኒያት ችግሮች ሲመጣባቸው፡ የሚኖራቸው ግንዛቤ፡ ችግሩን ያመጣባቸው፡ እግዚኣብሔር እንደኾነ ነው። ከዚያም ከገጠማቸው ችግር የሚገላገሉ የሚመስላቸው፡ ፆም፣ ጸሎት፣ ስግደት የተባሉትን የትሕርምት ስልቶች፡ ኣድካሚ በኾነ ኹኔታ በሚፈጽሙበት ጊዜ፡ ያን ድካማቸውን እግዚኣብሔር ተመልክቶ፡ እርሱ ያመጣው ስለኾነ እርሱ ራሱ እንዲሚያስወግደው ነው። ነገር ግን፡ እውነታውን ስናየው፣ ማንም ኣስተዋይ ሰው በቀላሉ እንደሚግነዘበውም፡ እንደዚህ ዓይነት የመፍትሔ ርምጃ፡ የተከሰተውን ችግር ኣያቃልለውም፤ ሥነ-ፍጥረትም እንዲህ ኣይደለም የተሠራችው! በእንደዚህ ዓይነት ኹኔታም ኣይደለም የምትተዳደረው! ይልቁኑ ችግሩን ለመፍታት መደረግ ያለበት፡ የችግሩን ምንነትና ማንነት በጥንቃቄ መከታተልና ማወቅ ነው። ከዚያም፡ የመፍትሔው ኣግጣጫ፡ ከዚያው ችግሩን ከመገንዘቡ ሂደት ይመነጫል። ነገር ግን ብዙ ሰዎች፡ ይህንን ዓይነቱን ችግሮችን ለማቃለልና ለማስወገድ የሚያስችልውን የመፍትሔ ኣወሳሰድ መንገድ ውስጥ ለመግባት ልምድ ወይም ትዕግስት የላቸውም፤ ስለዚህ ስለገጠማቸው ችግር ምንም ዓይነት ዕውቀት የላቸውም። ፆም፣ ጸሎት፣ ስግደት የመሳሰሉት የትሕርምት ስልቶች እንግዲህ፡ ጥቅማቸው እዚህጋ ነው። እነዚህን ስልቶች በመጠቀም፡ ትዕግስትን፣ በኣንክሮ ማዳመጥን፣ መንስኤንና ውጤትን ማያያዝና መመርመርን፣ ባጠቃላይ በንቃት መከታተልን መጎናጽፍ ይቻላል።

## ዕፀ-በለስን መብላት።

በኔ በኩል፣ ከላይ በዝርዝር ባቀረብኩት ግንዛቤዬ መሠረት፡ መንፈስና ዕውቀት ኣንድ ኣይነት ጽንሰ-ሓሳቦች ናቸው። ስለዚህ፡ ሰዎች ኹሉ፡ የመጀመሪያዎቹ የኾኑትን ኣዳምና ሔዋንን ጨምሮ፡ ሲፈጠሩ ጀምሮ፡ ከዚህ ጸጋ ጋር ኣብረው ተፈጥረዋል (ምክኒያቱም ይህ ጸጋ፡ የነፍስ ጸጋ ነውና)። ማለትም በኣዳምና ሔዋን ኑሮ ውስጥ፡ ከዚህ ጸጋ ውጭ ኖረው የነበሩበት ጊዜ የለም ማለት ነው።

---

*[፭] ሐሪም፤ ሞት፤ (ሐረም፣ የሐርም፣ ይሕርም። ዐረ፡ ሐረመ፤ ከለከለ)፤ መተው፣ መጾም፣ ሕርም ማለት፣ ሰውነትን ከሚገባ ነገር መከልከል፤ ወይም  መራቅ፤ ከልካይና ተከልካይ መኾን፤ በብፅዐት በፈቃድ። ኪዳነወልድ ክፍሌ (፲፱፻፵፰ ዓ.ም.) መጽሓፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሓዲስ፤ ገጽ ፬፻፹፪።*

አሪት ዘልደት በተባለው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ውስጥ፡ ኣዳምና ሔዋን ዕፀ-በለስ የተባለችውን ዕፅ መብላታቸውንና ዕፀ-በለስን በመብላታቸው ምክኒያት፡ ፈጣሪያችን እግዚኣብሔር፡ "ከፉውንና ደጉን ለማወቅ ከእኛ እንደኣንዱ ኾኑ!" የሚለውን ንግግር እንዳሰማ ይገልጻል። በዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት መዝገብ ክፍል ውስጥ፡ ዕፀ-ሕይወት የተባለች ዕፅና እባብ የተባለችው እንስሳም ኣብረው ተጠቅሰዋል። እነዚህ ፍጥረታት፡ በዚህ የመጽሓፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ፡ በተምሳሌታዊነት ካልኾነ በቀር፡ በተፈጥሮአዊ ማንነታቸው በዚያ ቦታ ላይ በተጠቀሱበት መልክ የሚገኙ እንዳልኾኑ፡ አሁን በእነዚሁ ፍጥረታት ላይ እየኾነ ያለውን በማየት በቀላሉ መገንዘብ እንደሚቻል ይታወቃል፤ ይኸውም፡ እባብን "ተንኮለኛ"፣ ዕፀ በለስን "ዕውቀት የምትሰጥ ዛፍ"፣ ዕፀ ሕይወትን ደግሞ "የሕይወት ዛፍ" ተብለው የተጠቀሱት ኣገላለጾች ናቸው።

በኔ በኩል እንደተገነዘብኩት፡ የዕፀ-በለስ ተምሳሌትነት፡ ኣዳምና ሔዋን፡ የእውነትን ዕውቀት የመገንዘብ ብቅዓት ላይ መድረሳቸውን የሚያመለክት መኾኑ ነው። እንደሚታወቀው ኣዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ፡ ምንም እንኳ ነፍስ ያውቁ ሊኾኑ እንደሚችሉ ቢታመንበትም፡ ከመነሻው ጀምሮ በዓዋቂነት መንፈስ ኖረውበት ላይገኙ ይችላሉ። ነገር ግን፡ በቆይታ ውስጥ፡ የሕይወት ልምዳቸው፡ ዓዋቂዎች፣ ማለትም የእውነትን ዕውቀት የሚያውቁ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንግዲህ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ነው፡ እነዚህ ሰዎች፡ "ከፉውንና ደጉን ለማወቅ እንደእኛ ኾኑ!" ሊባልላቸው የሚገባው። ከመጻሓፉ ኣገላለጽ እንደምንረዳው ከኾነ፡ በተለይም ዕፀ-በለስ በእግዚኣብሔር ትእዛዝ ኣውጪነትና ኣስተላላፊነት፣ ሞትን የምታመጣ በመኾኗ፡ "እንዳትትበላ የተከለከለች የዕፅ ዓይነት ነች!" መባሉና እባብ የተባለችው እንስሳ ደግም፡ "በክፉት ተሞልታ፣ ኣዳምና ሔዋን እንዲሞቱ ኣስባ፡ እንዲበሉት መከረች!" የተባሉት ተምሳሌታዊ ኣገላለጾች የሚያመለክቱት፡ ኣዳምና ሔዋንን ለዓዋቂነት ያበቃቸው፡ መሳሳትና ማጥፋትን ጭምር የሚያከብረውና የሚፈቅደው፣ ፍጥረቱን ወይም መንግሥቱን ከሚያስተዳድርበት መርኅ የሚገኘው፣ የተፈጥሮ ነጻነት የተባለው የያንዳንዳቸን ጸጋ መኾኑን ነው። ምክኒያቱም፡ በያንዳንዳችን ላይ እንደሚታየው፡ ስህተትና ጥፋት፡ እንደዓይነቱ፣ መጠኑና ኹኔታው፡ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት የተለያየ ቢኾንም፡ በንቃት ለተከታተሉት ኣስተማሪነቱ ኣስተማማኝ ነው፤ ይኸውም፡ በጽድቅ ምግባር ሲኖሩ ለነበሩት ሰዎች፡ የክፉትን ኣኗኗር ኹኔታና ስሜት በማሳየት፡ የጽድቅ ሕይወታችውን የደስታ ምንነት የማስገንዘብ ዕድል መፍጠሩ ነው።

ኪዳናዊ ዮሓንስ ደጉ፤

መስከረም ፲፪፣ ፳፻፱ ዓ.ም።

*ዋቢ የኾኑ መጻሕፍት ስም ዝርዝር።*


፩. *ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ (፲፱፻፺፫ ዓ.ም.)*፤ **ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!**፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

፪. *ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ (፲፱፻፺፮ ዓ.ም.)*፤ **ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት። የተደበቁ ምሥጢሮች የተገለጡበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት፣ አንደኛ መጽሓፍ**፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

፫. *ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ (፲፱፻፺፯ ዓ.ም.)*፤ **ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት። የተደበቁ ምሥጢሮች የተገለጡበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት፣ ኹለተኛ መጽሓፍ**፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

፬. *ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ (፲፱፻፺፰ ዓ.ም.)*፤ **ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት። የተደበቁ ምሥጢሮች የተገለጡበት እና የሕይወት ጥያቄዎች የተመለሱበት፣ ሦስተኛ መጽሓፍ**፤ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

፭. *ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ (፳፻፮ ዓ.ም.)*፤ **ኣዳምና ሔዋን በኢትዮጵያ! ኢትዮጵያዊው በጦቢያ ፍለጋ! ፩ኛ መጽሓፍ።** ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።

፮. *ኣለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ (፲፱፻፵፰ ዓ.ም.)*፤ **መጽሓፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሓዲስ**፤ ኣለቃ ደስታ ተክለወልድ።